April 8, 2016

ውድ Cambridge Public Schools (CPS) ቤተሰቦች እና ማኅበረሰብ፣

ከ3ኛ-እስከ10ኛ ክፍል ያሉ ሕፃናት በየዓመቱ በፀደይ የሚወስዱትን ፈተና በተመለከተ ማሳወቂያዎች እና ወቅታዊ መረጃዎችን ልሰጣችሁ ነው። ለ 18 ዓመታት፣ CPS ተማሪዎች *MCAS* Massachusetts Comprehensive Assessment System -ማሳቹሴትስ የተሟላ ፈተና ሥርዓት) የተሰኘ የእርሳስ-እና-ወረቀት ፈተና በፀደዩ ወቅት ሲወስዱ ቆይተዋል። በመጪው በልግ፣ ቤተሰቦች የልጆቻቸው የፈተና በክፍል ደረጃው የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣታቸውን እንዲያውቁ ሪፖርቶች ተልኮላቸዋል። መንግስትም የዚህን ፈተና ውጤት የትምህርት ቤት ክልሎች ስኬታማ ለመሆን ተጨማሪ ወይም የተለየ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት እንዲችሉ ለማገዝ ተጠቅሞበታል።

በሚቀጥሉት ሁለት አመታት ውስጥ፣ ሁሉም የማሳቹሴትስ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ወደ *በኮምፒውተር* ወደሚታገዝ ፈተና ይዛወራሉ፣ ይህም በተለምዶ MCAS 2.0በመባል የሚታወቀው ነው። አሁንም በመሰራት ላይ ያለ ሲሆን፣ MCAS 2.0 is በብሔራዊ ደረጃ በተዘጋጀው PARCC (Partnership for Assessment of Readiness for College and Career - ትብብር ለኮሌጅ እና ሙያ ዝግጁነት ፈተና ) የተሰኘ ፈተና ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ ነው።

MCAS 2.0 እስከ 2017 ፀደይ ድረስ ለትግበራ ዝግጁ አይሆንም። ለሽግሩ ለመዘጋጀት፣ የትምህርት ቤቶች የቀድሞውን MCAS በዚህም አመትም መጠቀም ይፈልጉ እንደሆነ ወይም PARCCን ማካሄድ ይፈልጉ እንደሆነ አማራጭ ተሰጥቷቸዋል። የCambridge School Committee ተማሪዎቹን ለ2017MCAS2.0 በተሻለ ለማዘጋጀት PARCCን በዚህ አመት ለማካሄድ ድምፅ ሰጥቷል።

በዚህ ደብዳቤ ግልባጭ የ2016 የፀደይ ፈተና መርሐግብር ተካቷል፣ ይኸም የትኞቹ ትምህርት ቤቶች PARCCን በኮምፒውተር እንደሚወስዱ እና የትኞቹ ደግሞ ለአንድ ተጨማሪ ዓመት በወረቀት እና በእርሳስ እንደሚወስዱ የሚገልፀውን መረጃ ያካትታል።

ደረጃ የወጣላቸው ፈተናዎች ለሁላችንም ብዙ ጥያቄዎችን እና ሃሳቦችን ያስነሳሉ። ለዚህም ማ'ዕከላዊ የሆነ ድርጣቢያ በተደጋጋሚ ጥያቄዎች እና ስጋቶች ዙሪያ አዘጋጅተናል። አገናኙ በዋናው ድርጣቢያችን www.cpsd.us ላይ ተለጥፏል። በስቴት አቀፉ ፈተና የልጅዎን ተሳትፎ በተመለከተ ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ የትምህርት ቤቱን ኃላፊ ያነጋግሩ።

## ስቴት አቀፍ ፈተናዎች:
**Cambridge Public Schools Transition Plan**

**2014-15:** MCAS

**2015-16:** PARCC *እንግሊዝኛ ቋንቋ፣ ኪነጥበብ እና ሂሳብ*
- 10ኛ ክፍል: MCAS
- ሳይንስ: MCAS

**2016-17:** MCAS 2.0

እንደ ሁልጊዜው፣ መምህራኖቻችን እና አስተዳዳሪዎቻችን ይህንን ለዚህ ለውጥ ለመዘጋጀት ባሳዩት ትጋት የሚሰማኝን ከፍተኛ ኩራት መግለፅ እወዳለሁ። እንዲሁም እርስዎ የልጅዎን ትምህርት እና የወደፊት ስኬት ለመደገፍ የምታደርጉትን ነገር ሁሉ አከብራለሁ።

የእርስዎ,

ጄፈሪ ኤም ያንግ
የትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

## ስቴት አቀፍ ፈተናዎች: የጊዜ ሰሌዳ እና አቀራረብ በትምህርት ቤት

| | |
|---|---|
| Amigos<br>Baldwin<br>Cambridgeport<br>Cambridge Street<br>Fletcher Maynard<br>Graham & Parks<br>Kennedy-Longfellow<br>King Open<br>Morse<br>Peabody<br>Rindge Avenue<br>Tobin<br>Vassal Lane | **የወረቀት** ሂሳብ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ PARCC<br>5ኛ ክፍል ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ MCAS<br>መርሐ ግብር ይለያያል ነገር ግን በአፕሪል 25 እና ሜይ 27 መካከል ይከናወናል |
| Haggerty<br>Martin Luther King<br>Putnam Avenue | **የኮምፒዩተር** ሂሳብ እና እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ PARCC<br>5ኛ ክፍል ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ MCAS<br>የጊዜ ሰሌዳ ይለዋወጣል ነገር ግን በአፕሪል 25 እና ጁን 6 መካከል ይከናወናል። |
| ካምብሪጅ ሪጅ እና ላቲን ትምህርት ቤት (ሁለተኛ ደረጃ) | 9th ክፍል ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ MCAS<br>10th ክፍል MCAS – የመመረቂያ መስፈርት |

## የግዴታ ፈተናዎች በክፍል ደረጃ

| ክፍል | የትምህርት አይነት |
|---|---|
| 3 | ማንበብ፣ ሂሳብ |
| 4 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት እና ስነፅሁፍ አፃፃፍ፣ ሂሳብ |
| 5 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት፣ ሂሳብ፣ and ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ/ምሕንድስና |
| 6 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት፣ ሂሳብ |
| 7 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት እና ስነፅሁፍ አፃፃፍ፣ እና ሂሳብ |
| 8 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት፣ ሂሳብ፣ and ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ/ምሕንድስና |
| 10 | እንግሊዝኛ ቋንቋ ኪነጥበብ አንብቦ መረዳት እና ስነፅሁፍ አፃፃፍ፣ ሂሳብ፣ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ/ምሕንድስና (* ይመልከቱ) |
| * | ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ጀማሪ ፊዚክስ፣ ወይም ቴክኖሎጂ/ምሕንድስና |

**ተጨማሪ መረጃ: www.cpsd.us**